**ወደ መተግበሪያው የመጀመሪያ መግቢያ**

የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ የምዝገባ ፎርም መሙያ መተግበሪያ ውስጥ ለመግባት ከታች የተገለፁትን እርምጃዎች መከተል ይኖርብዎታል።

መተግበሪያው ውስጥ በገቡ ቁጥር እርምጃ 1እና 2 ይታያሉ።.

**ይጠንቀቁ።** በግሪክ ህግ መሠረት ከ18 ዓመት በታች ከሆኑና ለእንክብካቤዎ ሃላፊነቱ ያለው አዋቂ ሰው አብሮት ከሌለ፣ የኤሌክትሮኒክ ፎርሙን መሙላት መቀጠል የለበትም። ሂደቱ እንዲፈፀም ወደ ሚመልከተው አገልግሎት መቅረብ ይኖርቦታል።

**<u>እርምጃ1: ማንነት ማረጋገጫ</u>**

| | |
|---|---|
| **የጥገኝነት ቅድመ ማመልከቻ(ቅድመ ምዝገባ) ቁጥር** | ከሚመልከተው አገልግሎት የተሰጠዎትን የጥገኝነት ቅድመ ማመልከቻ ቁጥር (ቅድመ ምዝገባ) ይምሉ። ይህም ቁጥር ከሚመልከተው አገልግሎት የተሰጠዎት ይፋዊ ሰነዶች ላይ ተፅፎ ይገኛል። |
| **የአያት ስም** | የመጀመሪያቹን ሁለት (2) የአያቶትን ስም ፊደላት በአብይ የእንግሊዝኛ ፊደላት ይምሉ። በመጀመሪያ ምዝገባ ሂደት ላይ ለሚመለከተው አገልግሎት ያሳወቁትንና የሚመልከተው አገልግሎት የሰጠዎት ይፋዊ ሰነድ ላይ እንደተጠቀሰው መሆን አለበት። |
| **ስም** | የመጀመሪያቹን ሁለት (2) የስሞትን ፊደላት በአብይ የእንግሊዝኛ ፊደላት ይምሉ። በመጀመሪያ ምዝገባ ሂደት ላይ ለሚመለከተው አገልግሎት ያሳወቁትንና የሚመልከተው አገልግሎት የሰጠዎት ይፋዊ ሰነድ ላይ እንደተጠቀሰው መሆን አለበት። |
| **የትውልድ ቀን** | የተወለዱበትን ቀን የመጀመሪያ የምዝገባ ሂደት ላይ ለሚመልከተው አገልግሎት እንዳሳወቁት ይምሉ።ቀን/ወር/ዓመተ ምህረት በሚለው መልኩ ይምሉ። ለምሳሌ 1 የካቲት 2000 ለሚለው 01/02/2000 ወይም 1/02/2000 በሚለው መልኩ መፃፍ ይኖርበታል። |
| **የሞባይል ስልክ ቁጥር** | መተግበሪያው ውስጥ መግባት የሚያስችልዎ አንድ ግዜ ጥቅም ላይ የሚውል ኮድ እንዲላክልዎት የሚፈልጉትን የግሪክ የሞባይል ስልክ ቁጥርዎን ይምሉ። መቀጠል እንዲችሉ ኮዱን እርምጃ 2 ላይ መሙላት ይኖርቦታል። |
| **ኮምቢተር አይደለሁም** | ምስሉ ላይ የሚያዩትን ምልክቶች (ቁምፊዎች) ይምሉ። ምልክቱ ንዑስ የእንግሊዝኛ ፊደላትንና ቁጥሮችን ያካተተ ነው። ጽሑፉን ለማንበብ የሚከብድ ከሆነ « እድሳት captcha» የሚለውን በመንካት ሌላ ጽሑፍ እንዲመጣ ማድረግ ይችላሉ። |

**<u>እርምጃ 2: የኮድ አገባብ</u>**

ከማንነት ማረጋገጫው ማያ ገፅ(screen) ላይ **«መግቢያ»** የሚለውን በመጫን፣ በተሳካ ሁኔታ ማንነትዎ ከተረጋገጠ በኃላ እርምጃ 1 ላይ ባሳወቁት የሞባይል ስልክ ቁጥር የተላከልዎትን ለአንድ ግዜ ጥቅም ላይ የሚውል ባለስድስት አሃዝ ኮድ እንዲሞሉ ይጠየቃሉ።

**<u>እርምጃ 3: ቋንቋ</u>**

አንድ ግዜ ጥቅም ላይ የሚውለውን ኮድ በተሳካ ሁኔታ ከሞሉ በኃላ ፎርሙን መሙላት የሚፈልጉበትን **ቋንቋ** ይምረጡ።

**ይጠንቀቁ:** ይህ አማራጭ የመጨረሻ ነው። ምናልባት መመዝገብ የሚፈልጉትን ቋንቋ መለወጥ ቢፈልጉ የተሞላው ፎርም በሙሉ ይደመሰስና እንደ አዲስ መሞላት ይኖርበታል።